
## ሙስና በከተማችን ላይ ከነገሰ የሚከተሉት ተጽእኖ ይበራከታሉ

- ኢ-ፍትሀዊነት ያስፋፋል፡፡
- የምርት ስርጭትን ያዛባል፤
- ዕድገትን ያደናቅፋል
- የመሰረተ-ልማት ጥራትን ቀንሳል፤
- የመዋዕለ-ንዋይ ፍሰትን ቀንሷል፤
- ህዝብ በመንግስት ላይ እምነት እንዳይኖረው ያደርጋል
- ልማትና እድገትን ወደ ኋላ ይጎትታል ብሎም አስተዳደራዊ መዋቅርን ያፈርሳል

## ለሙስና መከላከል አጋዥ የሆኑ የህግ ማዕቀፎች እና ደንቦች

1. አዋጅ ቁጥር 75/2014 የአዲስ አበባ የሥነ-ምግባር እና የፀረ ሙስና ከሚሽን መቋሚያ አዋጅ
2. አዋጅ ቁጥር 881/2007 የሙስና ወንጀልን ለመደንገግ የወጣው አዋጅ፣
3. አዋጅ ቁጥር 668/2002 የሃብት ማሳወቅና ምዝገባ አዋጅ፣
4. አዋጅ ቁጥር 699/2003 የወንጀል ጠቋሚዎች እና የምስክሮች ጥበቃ አዋጅ፣
5. ደንብ ቁጥር 8/2015 የአዲስ አበባ የሥነ-ምግባር እና የፀረ ሙስና ከሚሽን የሠራተኞች አስተዳደር ደ ን ብ
6. ቁጥር 9/2015 የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎች አሠራርና አደረጃጀት ለመወሰን የወጣ ደንብ
7. ደንብ ቁጥር 11/2015 የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነ-ምግባር ግንባታ እና ሙስና መከላከል አሰራር ደንብ
8. ደንብ ቁጥር 10/2015 አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንግስት መሥሪያ ቤት፣ የልማት ድርጅት እና ህዝባዊ ድርጅት ተሿሚዎች እና ሠራተኞች የሥነ- ምግባር ደንብ

## የሙስና መንስኤ




C (Corruption) = M(Monopoly Power) + D(Discretion) – A (Accountability

ሙስና = ገደብ የለሽ ሥልጣን + ውሳኔ ሰጪነት - ተጠያቂነት

---

በስነ ምግባር ሚዲያና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት


አድራሻ
በአራዳ ክ/ከ ወረዳ 1 ቸርችል ጎዳና ትንሳኤ ህንፃ 4ተኛ ፎቅ

ጥቆማ ለመስጠት
የነፃ ስልክ መስመር
8887
እንዲሁም በመስመር ስልክ
011 126 61 87
011 126 61 72

Addis Ababa Ethics and Anti-Corruption -ፀረ ሙስና
Addis Ababa Ethics Media
aanticoruption@gmail.com


# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን

## በሙስና መከላከል መረጃና ጥናት ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ

"ሙስና የጋራ ጠላታችን ነው፤ በሕብረት እንታገል!"

ህዳር 2016 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## የሙስና ትርጓሜ

ሙስና የሚለው ቃል "ኮራፕተስ" (corruptus) ከሚለው የላቲን ቃል የተገኘ ሲሆን የአማርኛ ቀጥተኛ ትርጉሙም መለየት ወይም መሰበር ማለት ነው፡፡ ስለሆነም እንደ ጽንሰ ሀሳብ ሙስና ማለት ከስነ- ምግባር፤ ከግብረገብነት፤ ከባህል፤ ከህግ፤ ከእምነት የወጣ ስነ ባህርይ ማለት ነው፡፡

## የኮሚሽኑ ራዕይ፣ ተልዕኮዎች፣ መርሆች

### ራዕይ

በ2025 ሙስና ለከተማ አስተዳደሩ ልማት እና መልካም አስተዳደር እንቅፋት ከማይሆንበት ደረጃ ማድረስ፡፡

### ተልእኮ

አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ትምህርትን በማስፋፋት፣ የአሰራር ስርአትን በማጥናትና እንዲሻሻሉ በማድረግ፣ ሙስናና ብልሹ አሰራርን በመከላከል በመንግስት አሰራር ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን ማድረግ፡፡

### የኮሚሽኑ ዓላማዎች

1. የሥነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ትምህርቶችን በማስፋፋት የሞራል እሴቶችን በመገንባት የነቃ እና ሙስናን ሊሸከም የማይችል ኅብረተሰብ መፍጠር፤
2. የሙስና ወንጀልን እና ብልሹ አሠራርን መከላከል፤
3. ነዋሪው የፀረ-ሙስና ትግል ባለቤት እንዲሆን ማድረግ፤
4. በጸረ ሙስና ትግል ብልሹ አሰራርን ለማስቀረት ግልጽና ተጠያቂነት ያለው አሰራር ሥረዓት ማስፈን፤
5. በህግ የተሰጡትን ስልጣንና ተግባር ለመፈጸም የሚያስችል ተቋማዊ አቅም መገንባት፡፡

## የሙስና መከላከል መረጃና ጥናት ዳይሬክቶሬት የሚሰጡ ዋና ዋና አገልግሎቶች

- የሙስና መረጃ ቅበላ አማራጭ ስልቶችን እንዲስፋፋ፤ እንዲዘምን እና ለህ/ሰቡ እንዲተዋወቅ ማድረግ፤
- በብልሹ አሰራርና ሌብነት ላይ የሚቀርቡ ጥቆማዎችን መቀበል፣ መተንተንና ማጥናት ማድረግ፤
- የሙስና ተጋላጭነት ጥናት ማጥናትና/ እንዲጠና በማድረግ ያሉ ክፍተቶችን መለየትና የማሻሻያ ምክረ ሀሳብ በማቅረብ ተግባራዊነቱን መከታተል
- የዘርፍ ተኮር የሙስና መከላከል ጥናት ማጥናት፤ ማስጠናት
- በከተማ አስተዳደሩ የሚከናወኑ ትላልቅ ፕሮጀክቶች፣ ግዢዎች፣ የሚፈጸሙ ውሎች ከሙስና እና ብልሹ አሠራር በፀዳ መልኩ እየተከናወኑ መሆናቸውን በጥናት መለየት፤
- በኮሚሽኑ በተሰሩ የጥናት ግኝቶችና ምክረ-ሃሳቦች ላይ ውይይት በማድረግ የጋራ መግባባት ላይ እንዲደርስ ሁኔታን መፍጠር፣
- የአስቸኳይ የሙስና መከላከል ስራን መስራት መከታተል እና መገምገም፤
- የጠቋሚዎች የህግ ከለላ ጥያቆዎችን በመቀበል እና በማደራጀት መፍትሄ እንድያገኙ በማሣወቅ መደገፍ
- ሙስናን በመከላከልና ተጠያቂነትን በማስፈን ረገድ ከፍትህ ተቋማት ጋር በቅንጅት መስራት፤
- ከተማ አቀፍ የሙስና ተጋላጭነት ዳሰሳ ቅኝት በማድረግ የተቋማትን የሙስና ተጋላጭነት ደረጃ ማውጣትና የሙስና ተጋላጭነት ቅነሳ በጋራ ዕቅድ ማዘጋጀትና መተግበር

## የሙስና መከላከል ስራ መሰረታዊ አላማዎች

1 የህዝብና የመንግስት ሀብት ከምዝበራ ቀድሞ ለመከላከልና ተከስቶ ሲገኝም የተጠያቂነት ስርዓት እንዲሰፍን ለማድረግ፤

2 በየተቋማቱ ህጋዊ አሠራሮች ተከብረው ተግባራት እንዲፈፀሙና ለተገልጋዩ ህብረተሰብ ፍትሐዊ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል አሠራር እንዲከተሉ ለማድረግ፣

3 በየደረጃው የሚገኘው አመራርና ፈፃሚ ሙስናና ብልሹ አሠራርን በቁርጠኝነት እንዲታገል ለማድረግ፣

4 መልካም እሴቶች ተጠብቀው ተሻጋሪና ለሀገሩ ዘብ የሆነ ትውልድ እንዲፈጠር የትግል ምህዳሩን ማመቻቸት፤

5 በተቋማት የግልፀኝነትና የተጠያቂነት አሠራር እንዲሰፍን በማድረግ ብልሹ አሰራሮች እንዲወገዱና መልካም አስተዳደር እንዲጎለብት ማድረግ፣

6 የተቀናጀ የሙስና መከላከል ስትራቴጂን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ምቹ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣

7 ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ የተቀናጀ የሙስና መከላከል ስራን መስራት

8 በሳይንሳዊ የጥናትና ምርምር ስራዎች የሙስና ተጋላጭነት ችግሮችን መፍትሄ ለማበጀት፤

